የሰ/መ/ቁ. 70500

ታህሳስ 17 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሤ

**አመልካች፡-** ኢንጅነር አድማሱ ገብሬ (ገብሬ አድማሱ) ጠበቃ ገንዘቡ ገ/አምላክ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የፌዴራል ዐቃቤ ህግ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ክስ ሲሆን የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በተጠሪ ከሣሽነት ነው፡፡ ቀርቦ የነበረው ክስ ተከሣሽ የብሩክ ፊልምስ ኃላ/የተ/የግል ማህበር ባለቤት ከሆኑት የግል ተበዳይ አቶ ብሩክ መክብብ ጋር መንተዮቹ የሚል ርዕስ ያለው የአማርኛ ፊልም ለመሥራት ተዋውለው ሳለ የግል ተበዳይ ሳያውቁ በግል ተበዳዩ (ፕሮዲዩሰሩ) የተሠራውን ፊልም ከተጠናቀቀ በኋላ ከግል ተበዳይ ሠራተኞች ጋር በመመሳጠር ከተቀበለ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ በማምጣቱ እና ርዕሱን በመቀየር ‹‹ለአባቷ›› የሚል ርዕስ በመስጠት የፊልሙ ባለቤት ሳይሆን የፊልሙ ባለቤት በመምሰል ለህዝብ እይታ በማቅረብ የቅጅና ተዘማጅ መብቶችን ለመጠበቅ የወጣውን አዋጅ ቁ. 410/96 አንቀጽ 7(1)(ሀ) እና 36(1) ሥር የግል ተበዳይን የኢኮኖሚ መብት በመጣስ ተከሰዋል የሚል ነው፡፡

ተከሣሹ የቀረበበትን ክስ በመካድ የተከራከረ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት በዚሁ በተከሰሰበት ወንጀል ሥር ጥፋተኛ ነው በማለት የጥፋተኘነት ውሣኔ ከሰጠ በኋላ አመልካች በ2 ዓመት ከ6 ወራት እሥራት እንዲቀጣ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘቱ ይግባኙን ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት ካከራከረ በኋላ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በማጽናት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ የግራ ቀኙን ክርክር በጽሑፍ ሰምተናል፡፡ ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች፣ ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም አመልካች በተከሰሰበት የወንጀል ድንጋጌ ጥፋተኛ ተብሎ የተቀጣው በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ ተይዞ ጉዳዩ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚሁ መሠረት ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ በአሁኑ አመልካች እና የግል ተበዳይ መካከል የውል ግንኙነት ያለ ስለመሆኑ፣ በዚሁ የውል ግንኙነት መሠረት የግል ተበዳይ በአመልካች የሚቀርብለትን ድርሰት ወደ ፊልም ለመቀየር የተስማሙ ስለመሆኑ፣ በዚህ ስምምነት መሠረት ለመልካች ለሥራው ብር 800,000

ሊከፍልና የግል ተበዳይ ደግሞ ፊልሙን በማጠናቀቅ ለአመልካች የሚያስረክብና አመልካችም የፊልሙ ባለቤት እንደሚሆን የተሰማሙ ስለመሆኑ በበታች ፍ/ቤቶች በፍሬ ነገር የተረጋገጡ ነጥቦች ናቸው፡፡

በሌላ በኩል በግራ ቀኙ መካከል በዚሁ የውል ግንኙነት መሠረት ያደረገ የፍትሐብሔር ክርክር እስከዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ታይቶ በመዝ.ቁ. 69247 ላይ እልባት ያገኘ ሲሆን አመልካች የፊልሙ ባለቤት ነው በማለት የግልግል ዳኞች የሰጡት ውሣኔ እና በፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት የፀደቀው የውሣኔ ክፍል በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎትም ያልተነካ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በዚሁ የፍትሐብሔር ጉዳይ አከራካሪ ከሆነው ፊልም ግራ ቀኙ ያላቸው መብትና ግዴታ ምን እንደሆነ የተመለከተ ሲሆን ከሥራውም የሚገኘውን ትርፍ የሚከፋፈሉበትን አግባብ በተመለከተ ውሣኔ የተሰጠበት ስለመሆኑ ተገንዝበናል፡፡

ከላይ የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች ይዘን የወንጀል ኃላፊነት ለያቋቁሙ የሚችሉ ተግባራት ስለመፈፀማቸው መመልከቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ በዚሁ መሠረት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 23(2) መሠረት አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚያቋቁሙት ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ እንደሆነ ይደነግጋል፡፡ በዚሁ መሠረት አመልካች የተከሰሰበት የቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ ቁ.410/1996 አንቀጽ 7(1)(ሀ) መሠረት ለሥራው ባለቤት የተሰጠን ተግባር ባለቤት ሣይሆን ባለቤት በመምሰል ፈጽሟል በሚል ሲሆን አመልካች የፊልሙ ባለቤት ስለመሆኑ የግራ ቀኙ የተሰማሙበትን ውል መሠረት በማድረግ የግልግል ዳኞች የሰጡት ውሣኔ አልተሻረም፡፡ አመልካች የፊልሙ ባለቤት በተባለበት ሁኔታ ደግሞ የዚህ የወንጀል ህግ ድንጋጌ ተጥሷል ማለት አይቻልም፡፡ በሌላ በኩልም ባለቤት የሆነ ሰው ፊልሙን በእጁ አድርጎ መገኘቱ ከዚሁ ባለቤት ነኝ ከሚል ሃሣብ የተነሣ ከመሆኑ ባሻገር የወንጀል ተግባር ወይም የግል ተበዳይን የኢኮኖሚያዊ መብት በመጣስ ሃሣብ የፈጸመ ስለመሆኑ የወንጀል ሞራላዊ ፍሬ ነገር ስለመረጋገጡ የተደነገጉት የወንጀል ህግ ከአንቀጽ 57 እስከ 59 ደረስ ያሉት ድንጋጌዎች አያመለክቱም፡፡ በዚሁ መሠረት አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት የወንጀል ድንጋጌ ሥር የሞራላዊም ሆነ የህግ ፍሬ ነገሮች ባልተረጋገጠበት ሁኔታ በመሆኑ ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣቱ አግባብነት የሌለውና ወንጀሉን የሚያቋቁሙ ፍሬ ነገሮች ባልተሟላበት በመሆኑ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡

ባጠቃላይ በአመልካችና በግል ተበዳይ መካከል ያለው ግንኙነት የውል አፈፃፀምን የሚመለከት የፍትሐብሔራዊ ባህሪይ ያለው በመሆኑ አመልካች በተከሰሰበት የወንጀል ድንጋጌ ሥር ሕጋዊ ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣቱ አግባብነት የሌለውና መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1/ የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ. 59998 ሰኔ 23 ቀን 2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ.74529 በቀን 19-12-2002 ዓ.ም እና በቀን 21-12-2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 195(2(ለ(1)) መሠረት ተሽሯል፡፡

2. አመልካች በተከሰሰበት የወንጀል ድንጋጌ ሥር ሕጋዊና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች ባልተሟሉበት ሁኔታ ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣቱ አግባብነት የለሌውና መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ከክሱ በነፃ እንዲሠናበት ብለናል፡፡

3. አመልካች በሌላ የወንጀል ጉዳይ የማይፈለግ ከሆነ ከማረሚያ ቤት እንዲለቀቅ ለሚመለከተው ይፃፍ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሐ/አ